

# ሻ __________ ማ

*ሥርጉተ ሥላሴ*

ሻ __________________ ማ
ባለ ሸማ።
ሻማ _________ ዛላማ
ባለ-ቃል ______ ለዛማ

ለእማ _________ ለእማማ።

ሻ __________________ ማ
ባለ ሸማ።
ሻማ _________ ዛላማ
ባለ-ቃል __________ ለዛማ
ለእማ ______ ለእማማ።

ሻማዋ መስዋትነትን ተሻምታ
ፍቅርን በዝቀሽ ሸምታ
***ተስፋን ቀለበች ፅናትን አቅንታ!***

ሻ _____________________ ማ
ባለ-ሸማ።
ሻማ _________ ዛላማ
ባለ-ቃል ___________ ለዛማ

የአንስትን እኩልነት አብርታ
ዕብለትን በሀቅ ንድፍ በሳስታ
ግለኝነትን፣ አፈርሳታ አውጥታ!

... 2

ሻ ______________________ ማ
ባለ ሸማ።
ሻማ ________ ዛላማ
ባለ-ቃል _________ ለዛማ
ለእማ ______ ለእማማ።

ኀባጣን ልታቃና
ኀሰኝነትን ልትቀጣ
የሚዲቅሳ አብራክ ልበ-ቀና!

ሻ _______________________ ማ
ባለ ሸማ።
ሻማ ___________ ዛላማ
ባለ-ቃል ____________ ለዛማ
ለእማ ________ ለእማማ።

የሃልዬ እናት አውራ
የታማኝነት ልዩ ወጋግራ!

*ታህሣሥ 29 ቀን 2001 ዓ.ም. ሂርሸን ሆቴል*
*ሥጦታ፡ ለክብርት ዳኛ ብርቱካን ሚደቅሳ የአንድነት ሊቀመንበር*